## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



አሰፋና ቤተሰቦቹ

### ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ::

ምሳሌ፦ ወር → አንድ ወር ሰላሳ ቀናት አሉት::

1. አፈር  2. እርሻ  3. እርከን

### ውስብስብ ፊደላት

| | | |
|---|---|---|
| ኰ | ኲ | ኴ |

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ::

| | | |
|---|---|---|
| ኰ | ኲ | ኴ |

### ማጣመር

ሀ. ፊደላቱን አጣምራችሁ ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ::

1. ኰ ለ ኰ ለ  2. ኲ ል  3. ኰ ተ ኰ ተ  4. ኲ ር ኲ ም


ለ. ቃላቱንና ፊደላቱን አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ::

ምሳሌ፦ ደፈነ-ች → ደፈነች

1. ፈለገ-ች  2. ጠራ-ች  3. ደረሰ-ች  4. ላከ-ች  5. በለጠ-ች

## ግለንባብ

### ብልኋ ጉንዳን



በአንድ ወቅት አንዲት ብልህ ጉንዳን ነበረች:: ሳታስበው አቶ ምስጥ ዘው ብሎ ወደጉድጓዷ ገባ:: ምግብም እንድትሰጠው ጠየቃት:: ጉንዳንም “ምን ችግር አለው? እሰጥሃለሁ፤ አሁን ግን መጋቢት ስለሆነ እኔም አንተም ፈላልገን እንበላለን፤ በሰኔና በሐምሌ በበጋው ያጠራቀምኩትን እንጋራለን” አለችና ሰደደችው:: ወዲያው ግንቦት እንዳለቀ ጉድጓዷን ደፈነች:: ምስጥም መግቢያ አጣ፤ መስከረምም ጠባ::

## 2ኛ ቀን

## ውስብስብ ፊደላት

| | |
|---|---|
| ኳ | ኴ |

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ::

| | |
|---|---|
| ኳ | ኴ |

## ማጣመር

ፊደላቱን አጣምራችሁ ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ::

ኳ ስ　　ኳ ኳ ቴ　　ታ ን ኳ　　ድ ን ኳ ን

## አንብቦ መረዳት


ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ::

1. ምስጥ ወደጉንዳን ጉድጓድ የመጣው ለምንድን ነው?
2. ብልህነት ይጎዳል ወይስ ይጠቅማል? ለምን?

## ቃላት

በክፍት ቦታዎች ተስማሚ ቃላትን እያስገባችሁ ፃፉ።

ምሳሌ$_1$ ብልህ ልጅ። ምሳሌ$_2$ ታታሪ ሰው




## መፃፍ

በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት መርጣችሁ በማጣመር ዓረፍተነገር ፃፉ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አየለች | ነው | ጐበዝ | ታታሪ | ከድር |
| ናት | ስመኘው | ፋጡማ | አዋቂ | |

ምሳሌ፦ አየለች ጎበዝ ናት።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### አሰፋና ቤተሰቦቹ

## ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. አረም 2. መባቻ 3. ማብቂያ 4. ባለቤት

## ውስብስብ ፊደላት

| | | |
|---|---|---|
| ጐ | ጒ | ጔ |

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

| | | |
|---|---|---|
| ጐ | ጒ | ጕ |

## ማጣመር


ፊደላቱን አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ጐ ረ ም ሳ　　ጐ ብ ኚ　　ጒ ር ጥ　　ጕ ል ት

## ግለንባብ

### የዓመቱ ወራት

አንድ ዓመት አስራ ሁለት ወራት አሉት። እነሱም፣ መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር፣ ታህሳስ፣ ጥር፣ የካቲት፣ መጋቢት፣ ሚያዝያ፣ ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሐምሌና ነሐሴ ናቸው። በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ጳጉሜ አስራሶስተኛ ወር ተብላ ትቆጠራለች።




## 4ኛ ቀን

## ውስብስብ ፊደላት

| | |
|---|---|
| ኋ | ጌ |

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ።

| | |
|---|---|
| ኋ | ጌ |

## መነጠል

ፊደላቱን ነጥላችሁ ፃፉና አንብቡ

ምሳሌ፦ ጓሮ → ጓ ሮ

ጓል ጓጓ ጓዝ ጓያ ጓዳ

## አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. በአንድ ዓመት ውስጥ ስንት ወራት አሉ?
2. በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር አስራሶስተኛዋ ወር ማን ናት?
3. የዓመቱን ወራት በቅደምተከተል ተናገሩ?

## ቃላት

በማቃረን አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| በጋ | ሀ. ጠቀመ |
| መጣ | ለ. ከፈተ |
| ጎዳ | ሐ. ሄደ |
| ደፈነ | መ. ክረምት |
| አገኘ | ሠ. አጣ |

## መፃፍ

በቃላቱ ዓረፍተነገር ፃፉ፡፡

1. ጳጉሜ → ጳጉሜ አስራሶስተኛ ወር ናት፡፡
2. ዘመን
3. በጋ
4. ክረምት

# 6ኛ ሳምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**አደይ**

### ቃላት

በድርጊት ቅደምተከተል መሠረት ክፍት ቦታዎችን ሙሉ።

ምሳሌ፦ አበባና ጓደኛዋ ተያዩ።

1. አበባና ጓደኛዋ ________።
2. አበባና ጓደኛዋ ________።
3. አበባና ጓደኛዋ ________።
4. አበባና ጓደኛዋ ________።

ድርጊት አመልካች ቃላት።

- ተሳሳሙ
- ናፍቆታቸውን ተወጡ
- ተገናኙ
- ተቃቀፉ

### ማጣመርና መነጠል

1. በምሳሌው መሠረት -ች ን በመጨመር አጣምራችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ ሠጠ + ች → ሠጠች

1. ሠራ 2. በላ 3. ሄደ

2. በምሳሌው መሠረት -ች ን እየነጠላችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ ሳመች → ሳመ - ች

1. ጠራች 2. ነዳች 3. ጠበቀች 4. አቀፈች

# ግለንባብ

## ስራ ጠባቂዎች

የነብርሃኑ ሰፈር ወጣቶች ወቅታዊ ሰብሎችን ጠብቀው የሚነግዱ ናቸው፡፡ ጊዜው ክረምት ነው፡፡ የበቆሎ እሸት ንግዱ ተጧጡፏል ፤ የባቄላና አተር እሸት ገበያም ደርቷል፡፡ በዚህም ሁኔታ ወጣቶቹ የክረምትና የፀደይ ወቅቶችን አሳለፉ፡፡ በጋው ተተካ፤ እሸቶችም ደረቁ፡፡ እነብርሃኑ የሚሸጡት ማግኘት አልቻሉም፡፡ ስለዚህ ወጣቶቹ በችግሩ ላይ ተወያዩ፡፡ በብድር ገንዘብ አገኙ ፤ በብሎኬት ማምረት ስራም ተሰማሩ፡፡



## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. ስራ ጠባቂዎች እነማን ናቸው?
2. የነብርሃኑ ሰፈር ወጣቶች ምን ችግር ገጠማቸው?
3. የነብርሃኑ ሰፈር ወጣቶች ለችግራቸውስ ምን መፍትሔ አገኙ?
4. ወቅት ጠብቆ መነገድ ምን ጉዳት ያመጣል?

### ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሥሩ፡፡

ምሳሌ፡- እሸቱ ደርቋል፡፡

1. በቆሎው  2. ንግዱ  3. ዝናቡ  4. ገበያው

## መፃፍ

የሥርዓተነጥብን ስያሜ ፃፉ።

| | | ሥርዓተነጥብ | ስያሜው |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ → | | : | ሁለት ነጥብ |
| | ሀ. | ፣ | |
| | ለ. | ። | |
| | ሐ. | ? | |

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### አደይ

## ቃላት

ሳጥኖቹን በተገቢ ቃላት ሙሉ።

- ቃላት
  - መኸር → ጥቅምት
  - በጋ → ______
  - በልግ → ______
  - ክረምት → ______

## ማጣመር

በምሳሌው መሠረት በክፍት ቦታዎች ቃላት አስገቡ።


ምሳሌ፡- አል-ዘነበ-ም → አልዘነበም

1. አል ____ ም  2. አል ____ ም  3. አል ____ ም

## ግለንባብ

### የዓመቱ ወቅቶች

አንድ ዓመት አራት ወቅቶች አሉት:: እነሱም መኸር (መፀው)፣ በጋ (ሀጋይ)፣ በልግ (ፀደይና) ክረምት በመባል ይታወቃሉ:: መስከረም፣ ጥቅምትና ህዳር የመኸር ወቅት ናቸው:: የበጋ ወቅት ታህሳስ፣ ጥርና የካቲት ሲሆኑ፣ የበልግ ወቅት ደግሞ መጋቢት፣ ሚያዝያና ግንቦት ናቸው:: ሌሎቹ ሰኔ፣ ሐምሌና ነሐሴ የክረምት ወቅት ይባላሉ::




## 4ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

**ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ::**

1. በአንድ ዓመት ውስጥ ስንት ወቅቶች አሉ? ስማቸውን ተናገሩ::
2. የበጋ ወቅት የምንላቸውን ወሮች ዘርዝሩ::
3. በመኸር(መፀው) ወቅት በአካባቢያችሁ ምን ምን ለውጦችን ታያላችሁ?

## ቃላት

**ዓረፍተነገር ፃፉ::**

ምሳሌ፦ ዝናብ → ዝናብ በክረምት ይዘንባል::

1. ክረምት 2. በልግ 3. መኸር 4. በጋ

## መፃፍ

በዓላቱ የሚከበሩባቸውን ወሮች ፃፉ።


ምሳሌ፦ የዘመን መለወጫ = መስከረም

ሀ. ፋሲካ    ለ. አረፋ    ሐ. መውሊድ    መ. ጥምቀት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የዛፍ ጥቅም**





### ቃላት

**በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡**

ምሳሌ፦ ድርቅ → ድርቅ ሰዎችን ይጎዳል፡፡

1. አውሎንፋስ  2. ዛፍ  3. አፈር  4. ወንበር

### ማጣመር

**የጎደሉትን ፊደላት በማሟላት ቃላት መስርቱ፡፡**

ምሳሌ፦ መጽ ሐ ፍ → መጽሐፍ

1. ጉድ_ _  3. ድር_ _  2. እው_ _  4. ግብ_ _  5. ክረ_ _

### ግለንባብ

**"ሠርገኛ መጣ...."**

ጊዜው ውድቅት ነው፡፡ ኃይለኛ ዝናብ ይጥላል፡፡

"በዛብህ! በዛብህ! ኧረ በዛብህ!" ተጣራች ባለቤቱ ማለፊያ፡፡



"ምን ሆንሽ?" አለ በዛብህ፡፡

"ውይ! አንተዬ አይታይህም እንዴ?"

"ምኑ?"

"ቤቱ ውስጥ ጎርፍ ገብቶ!"


"ውይ! ውይ! እንዴት ጉድ ተሰራን! በይ ነይ ተከተዪኝ፤ 'ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ' አለ ያገሬ ሰው" አለና ዝናብ እየመታቸው የጎርፍ ማፋሰሻ ቦይ መቆፈር ጀመሩ፡፡

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. የታሪኩ ባለቤቶች እነማን ናቸው?
2. እነበዛብህ ቤት ጎርፍ የገባው ለምን ይመስላችኋል?
3. “ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ” ከሚለው አነጋገር ምን ትረዳላችሁ?



### ቃላት

**ባለሁለት ፊደላት ቃላት መሥርቱ፡፡**

ምሳሌ፦ ጠላ፣ መታ፣ መጣ



### መፃፍ

**በምሳሌው መሠረት ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፦ እርከን ይሠራል ካልን፣


1. መፅሐፍ 2. ገበያ 3. ፅሑፍ 4. ግድብ

## 3ኛ ቀን



### ማዳመጥ

**የዛፍ ጥቅም**



## ማጣመር

ሀ. ወደብዙ ቁጥር ለውጡ።

ምሳሌ፡- በይ → በዮች

1. ዛፍ 2. እርከን 3. ወንዝ 4. ቋስ

ለ. ፊደላቱን በመምረጥና በማጣመር አስር ቃላት መስርቱ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አ | በ | ጠ | ረ | |
| ዘ | መ | ቀ | ወ | ምሳሌ፡- አደረሰ |
| ጋ | ለ | ደ | ሰ | |
| ጀ | ከ | ገ | ፈ | |

## ግለንባብ

### ጎርፍ መከላከል



ጎርፍ በተፈጥሮ የሚከሰት አደጋ ነው። በክረምት ወቅት ወንዞች ይሞላሉ፤ ጎርፍም ያስከትላሉ። በሰው ህይወት ላይ ችግር ያደርሳሉ። ንብረትን ያሳጣሉ። ቢሆንም የጎርፍ አደጋን መከላከል ይቻላል። በመጀመሪያ ዘዴዎቹን ማወቅ ተገቢ ነው፤ ለምሳሌ ዛፎችን መትከል፣ በዮችን ማዘጋጀት፣ እርከን መስራት ጥቂቶቹ ናቸው።

# 4ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

1. ጎርፍን ለመከላከል ምን ማድረግ ይገባል?
2. ከጎርፍ ውጪ የተፈጥሮ አደጋዎች ምን ምን ይመስሏችኋል?

## ቃላት

**የችግኝ አተካከል የድርጊት ቅደምተከተሎችን በትክክል ፃፉ፡፡**

ችግኝ ለመትከል → ቦታ ይመረጣል → ይመነጠራል → ☐ → ☐ → ☐


## መፃፍ

**የመማሪያ ክፍላችሁን ለማጽዳት ምን ምን ታደርጋላችሁ? በቡድን ተወያዩና የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም በቅደምተከተል በፅሁፍ መልሱ፡፡**

ሀ. በመጀመሪያ  ለ. በመቀጠል  ሐ. ከዚያ በኋላ  መ. በመጨረሻ

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



ብልጡ ቀበሮ

### ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡

ምሳሌ፦ ብልጥ → ቀበሮ ብልጥ እንስሳ ነው፡፡

1. ጉርሻ　　2. አይብ　　3. ነጋዴ

### ማጣመር


በፊደላቱ መነሻነት ባለሶስት ፊደላት ቃላትን ተናገሩ፡፡

ምሳሌ፦ ቀ → ቀበረ፣ ቀደሰ፣ ቀመሰ

1. ደ　　2. ከ　　3. መ　　4. ተ　　5. ለ

### ግለንባብ

#### መንገደኛውና ተኩላ



አንድ መንገደኛ ከዛፍ ግንድ ጋር የታሰረ ተኩላ ያገኛል፡፡ ተኩላውም "እባክህ ፍታኝ" ይለዋል፡፡ መንገደኛውም "ምን ገዶኝ" ብሎ ይፈታዋል፡፡ በመቀጠል ተኩላው "እበላሃለሁ" አለው፡፡ "በል ጦጢት ትፍረድና ትበላኛለህ" አለው፡፡ ከዚያ በኋላ ተያይዘው ወደ ጦጢት ሄዱ፡፡ ጦጢትም ሰውዬውን "መጀመሪያ ተኩላን ስታገኘው እንዴት ነበር? በድርጊት አሳየኝ" አለችው፡፡ ሰውዬውም አስሮ አሳያት፡፡ ጦጢትም "በል! ሰውዬ ዱላ ከእጅህ ተኩላ ከፊትህ" አለችው፡፡ ሰውዬውም ተኩላውን በዱላው ቀጥቅጦ ገደለው፡፡

# 2ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።**

1. ጦጣዋ በመጀመሪያ ምን ብላ ተናገረች?
2. መንገደኛውስ በመጨረሻ ምን አደረገ?
3. ከዚህ ተረት ምን ተማራችሁ?

## ቃላት

**በምሳሌው መሠረት ሌሎቹን ሃሳቦች በፅሁፍ አሟሉ።**

ምሳሌ፡- <u>ከብት</u> ብሎ <u>ከብት አርቢ</u> ካለ

1. እንጀራ 2. መዝሙር 3. ፀጉር 4. ሸማ 5. ጠላ

## መፃፍ

**የቃሎችን የቦታ ቅደምተከተል አስተካክላችሁ ዓረፍተነገር ፃፉ።**

ምሳሌ፡- ገዝቶ መጣ ቡና ከበደ → ከበደ ቡና ገዝቶ መጣ።

1. ተንኮለኛ እንስሳ ቀበሮ ነው
2. ዳኛ ሆነ ቀበሮ
3. አይቡን ጨረሰው በልቶ ቀበሮ

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ብልጡ ቀበሮ**

### ቃላት

**በነጠላ ቁጥር በቃላችሁ ግለፁ።**

ምሳሌ፡- መንገደኛዎች → መንገደኛ

1. ተኩላዎች 2. ጦጣዎች 3. ቀበሮዎች 4. ውሻዎች

### መነጠል

**በምሳሌው መሠረት ቃላቱን ነጥላችሁ ፃፉ።**

ምሳሌ፡- ተማሪዎች → ተማሪ + ዎች

1. አስተማሪዎች 2. ነጋዴዎች 3. ዘለላዎች 4. ዘማሪዎች

### ግለንባብ

**የራበው መንገደኛ**



ከእለታት አንድ ቀን የራበው መንገደኛ የአተር እሸት ያለበት ማሳ አገኘ። ቁጭ አለና አተሩን ከነልባሱ ሲበላ ቆዬ። ጠገብ ሲል ልባሱን እያነሳ መብላት ጀመረ። በጣም ሲጠግብ ደግሞ ከውስጥ የዘሩን ፍሬ እያወጣ መብላት ያዘ። የማሳው ባለቤት ከዛፍ ሥር ሆና ታየው ኖሮ "መንገደኛ እንደመጀመሪያውም እንደመጨረሻውም አትብላ፤ እንደመካከለኛው ብላ" አለችው ይባላል።

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።**

1. የራበው መንገደኛ በመጀመሪያ ምን አገኘ?
2. የማሳው ባለቤትስ መንገደኛውን ምን ብላ መከረችው?
3. ከተረቱ ምን ትምህርት አገኛችሁ?

### ቃላት

**ለጥያቄዎች በፅሁፍ መልስ ስጡ።**

ምሳሌ፦ ውሃ ቀዳች ካልን

1. እርሻ 2. ፅሁፍ 3. ጥናት 4. ግንብ 5. እንጨት

### መፃፍ

**የአተር እሸት ክፍሎችን ዘርዝራችሁ ፃፉ።**

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**የእንቆቅልሽ ምንነት**

### ማጣመር

ሀ. ቃላቱን በምሳሌው መሠረት በአሉታ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- አውቃለሁ → አላውቅም

1. እወዳለሁ 2. እመጣለሁ 3. እስቃለሁ 4. እፅፋለሁ

ለ. አጣምራችሁ ቃላትን በቃላችሁ መሥርቱ፡፡

1. እ ን ቆ ቅ ል ህ 2. ም ን አ ው ቅ ል ሽ

ሐ. አጣምራችሁ ፃፉና ቃላትን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- አዲስ + አበባ → አዲስ አበባ

1. ንፋስ + ስልክ 2. ሽሮ + ሜዳ 3.አዲስ + ከተማ

### ግለንባብ

## የትምህርትቤት ጓደኞች

እሱባለውና ነፃነት ጓደኞች ናቸው፡፡ ወደትምህርትቤት ሲሄዱ እንቆቅልሽ መጫወት ይወዳሉ፡፡



እሱባለው፡- “እንቆቅልሽ?”

ነፃነት፡- “ምን አውቅልህ?”

እሱባለው፡- “ስሄድ አገኘኋት ስመለስ አጣኋት?”

ነፃነት፡- “ጤዛ፡፡”

ነፃነት፡- “አባ ሲሏቸው ቆብ የላቸው?”

እሱባለው መልሱ ጠፋው። ነፃነት "ሀገር ስጠኝ" አለችው። "አዲስ አበባን ሰጥቼሻለሁ" አላት። "አዲስ አበባ ተቀምጬ ምን አጥቼ፤ ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ፤ አባጨጓሬ ነው። በል የእኔን ቦርሳ ተሸክመህ ትምህርትቤት ታደርሳለህ" አለችው።

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።**

1. ከጓደኞቻችሁ ጋር ምን ምን ዓይነት ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ?
2. እሱባለው ነፃነትን ምን ብሎ ጠየቃት?
3. ነፃነትስ ምን ብላ መለሰችለት?
4. እሱባለው የነፃነትን ቦርሳ ከትምህርትቤት ያደርሰዋል? ለምን?

### ቃላት

**ቃላቱን በአዎንታ ፃፉ።**

ምሳሌ፦ አልሰጠሁም → <u>ሰጠሁ</u>።

1. አልሠራሁም
2. አልበላሁም
3. አልተኛሁም
4. አልቀረሁም
5. አልጠጣሁም

### መፃፍ

**ሁለት ሁለት እየሆናችሁ እንቆቅልሽ ፃፉና በክፍል ጓደኞቻችሁ ፊት ተጠያየቁ።**

ምሳሌ፦ ሰይድ፦ እንቆቅልሽ?

ሔለን፦ ምን አውቅልህ?

ሰይድ፦ ስሄድ አገኘኋት ስመለስ አጣኋት?

ሔለን፦ ጤዛ።

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## የእንቆቅልሽ ምንነት

### ቃላት

በምሳሌዎቹ መሠረት ሥሩ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እኔ | እኛ | አንተ | አንቺ | እናንተ |
| እሄዳለሁ | እንሄዳለን | ትሄዳለህ | ትሄጃለሽ | ትሄዳላችሁ |
| እሱ | እሷ | እነሱ | | |
| ይሄዳል | ትሄዳለች | ይሄዳሉ | | |

ሀ. እመጣለሁ ለ. እሠራለሁ ሐ. እፅፋለሁ

### መነጠል

በምሳሌው መሠረት ሥሩ።

ምሳሌ፦ ተጠየቀ → <u>ተ</u> _ <u>ጠየቀ</u>

1. ተጨፈረ
2. ተቆፈረ
3. ተነጠለ
4. ተጨመረ
5. ተነገረ
6. ተመለሰ

### ግለንባብ

## የእንቆቅልሽ ይዘቶች

የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች እንስሳትን፣ ተክሎችንና ምግቦችን በሚመለከት ይቀርባሉ። በተጨማሪም የሰውነት አካላትንና ቁሳቁሶችንም በመጠቀም ጥያቄዎች ይቀርባሉ። ለምሳሌ “ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ”፣ “መሰላል ያላት ግን ሰው የማይወጣት”፣ “ሺ ዓይን አለው አጥንት የለው” ተብሎ ቢጠየቅ መልሶቹ በቅደምተከተል “ዓይን”፣ “ማሽላ” እና “እንጀራ” ይሆናሉ።

# 4ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

በምሳሌው መሠረት በክፍል ውስጥ እንቆቅልሽ ተጠያየቁ::


| | ጠያቂ | መላሽ |
|---|---|---|
| ምሳሌ፦ | 1. ፀጉሯን አበጥራ ገበያ የምትወጣ | ግራምጣ ወይም ሱፍ → ከተክል:: |
| | 2. አባ ሲሏቸው ቆብ የላቸው | አባጨጓሬ → ከእንስሳት:: |
| | 3. አራት እግር ያለው ወንዝ አይሻገር | አልጋ → ከቁሳቁስ:: |

## ቃላት

ቃላትን በማቃረን አዛምዱ::

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ቆመ | ሀ. ቀረ |
| 2. አገኘ | ለ. ተቀመጠ |
| 3. ሞተ | ሐ. ዳነ |
| 4. ወጣ | መ. ገባ |
| 5. መጣ | ሠ. አጣ |

ክቦቹን አሟሉ::




## መፃፍ

ዓረፍተነገር ፃፉ::

ምሳሌ፦ ተቀመጠ → ጀማል ከወንበር ላይ ተቀመጠ::

1. ተሸከመ  2. አጣ  3. አገኘ  4. ዘመረ

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

## የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ዓይነቶችና ጥቅማቸው

### ቃላት

**ቃላትን በምሳሌው መሠረት መስርቱ::**

ምሳሌ፦ ፍሬ ብለን ፍራፍሬ ካልን

1. ሥር  2. ቅጠል  3. ቅመም  4. ጥሬ

### ማጣመር

**የፊደላቱን ቦታ በመቀያየር ቃላት መሥርቱ::**

ምሳሌ፦ ቀሰለ → ሰቀለ፣ ቀለሰ፣ ሰለቀ

1. ለቀበ  2. ሰጠበ  3. ረጠመ  4. ረከመ

### ግለንባብ

#### የልደት ቀኔ



በልደት ቀኔ ትምህርት መኖሩ አናዶኛል:: ከትምህርትቤት ስመለስ ቤታችን አሸብርቋል:: በጠረጴዛው ላይ ሻማዎች ተደርድረዋል:: አንድ ትልቅ ዳቦም አለ:: የፍራፍሬ ዓይነቶች፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ፓፓዬ፣ ማንጎ፣ ሃብሃብ ህብር ሠርተው ቀርበዋል:: ልክ ወደቤት ስገባ ሁሉም ቤተሰቦቼ “መልካም ልደት!” እያሉ አጨበጨቡ:: እኔም ሮጬ የምወደውን ብርቱካን አነሳሁ::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

1. የልደት ቀናችሁን አክብራችሁ ታውቃላችሁ? ምን ምን ይዘጋጅላችኋል?
2. ተራኪዋ ወደቤት ስትገባ ቤተሰቦቿ ምን ብለው ተቀበሏት?
3. ተራኪዋ ሮጣ ብርቱካኑን ያነሳችው ለምን ይመስላችኋል?

### ቃላት

**ዓረፍተነገር ጻፉ፡፡**

ምሳሌ፦ ዘር → አርሶአደሩ ዘር ዘራ፡፡

1. ቅጠል 2. ሙዝ 3. ቆስጣ 4. ሰላጣ 5. ቀይስር

### መፃፍ

**ቃላትን በየምድባቸው ዘርዝሩ፡፡**

| ተ.ቁ. | ቅጠላቸው የሚበላ | ግንዳቸው የሚበላ | ፍሬያቸው የሚበላ | ሥራቸው የሚበላ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የአበሻ ጎመን | ሸንኮራ አገዳ | ብርቱካን | ካሮት |

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ዓይነቶችና ጥቅማቸው**

### ቃላት

ቃላትን በየምድባቸው ዘርዝሩ፡፡

| የምወዳቸው የምግብ ዓይነቶች | የማልወዳቸው የምግብ ዓይነቶች |
|---|---|

### ማጣመር

ፊደላቱን በማጣመር ድምፅ በማሰማት አንብቡ፡፡


ምሳሌ፡- ት - ላ - ት - ል → ትላትል

1. ሥ - ራ - ሥ - ር
2. ገ - ደ - ላ - ገ - ደ - ል
3. ብ - ረ - ታ - ብ - ረ - ት
4. ጅ - ላ - ጅ - ል

### ግለንባብ

**እኔ ማን ነኝ?**

ከፍራፍሬዎች እመደባለሁ፡፡ ቅርፄ ክብ ነው፡፡ ስበስል መልኬ ወደቢጫ ያደላል፡፡ ተልጬ እበላለሁ፡፡ በውስጤ ከስምንት እስከአስር የሚደርሱ ክፍልፋዮች አሉኝ፡፡ በየክፍልፋዮቹ ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዘሮች አሉ፡፡ ሰዎች ሲመገቡኝ በጣም የምጣፍጥና ጤና የምሰጥ ነኝ፡፡ እኔ ማነኝ?



## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ብርቱካን ምን ዓይነት ቅርጽ አለው?
2. ብርቱካን ሲበስል ምን ዓይነት መልክ ይኖረዋል?
3. ክብ ቅርጽ ያላቸውን ሌሎች የፍራፍሬ ዓይነቶች ተናገሩ?


### ቃላት


በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡

1. ብርቱካን 2. ፓፓያ 3. ሃብሃብ 4. ማንጎ 5. ሙዝ

### መፃፍ

ክቦቹን በተገቢ ቃላት አሟሉ፡፡



## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

ሐናና የምግብ ምርጫዋ

### ቃላት

ዓረፍተነገር ፃፉ።

1. መረጠች 2. ተደነቀች 3. መጠነች 4. ተመገበች

### ማጣመር

የጎደሉ ፊደላትን በማሟላት ቃላት መሥርቱ።

ምሳሌ፦ ወ _ ወ _ → ወረወረ፣ ወሰወሰ፣ ወለወለ

1. ቀ _ ቀ _ 3. ሰ _ ሰ _ 5. ፈ _ ፈ _

2. መ _ መ _ 4. ጠ _ ጠ _

### ግለንባብ

## የጓሮ አትክልት ቦታ አዘገጃጀት



የጓሮ አትክልት ቦታን ለማዘጋጀት የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል ማከናወን ያስፈልጋል። በመጀመሪያ የመትከያ ስፍራን መምረጥ ተገቢ ነው። በመቀጠል ቦታውን መመንጠር፣ መቆፈርና ደጋግሞ ማለስለስ ያስፈልጋል። በመጨረሻም መደብ ማዘጋጀትና የውሃ ማፋሰሻ ቦዮችን ማውጣት ይኖርብናል።

# 2ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

**ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።**

1. የጓሮ አትክልት ቦታን ለማዘጋጀት ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ?
2. የጓሮ አትክልት ተክላችሁ ታውቃላችሁ? ምን ምን?

## ቃላት

**ዓረፍተነገር ፃፉ።**

ምሳሌ፡- አጠበች → ዘይነባ ልብስ አጠበች።

1. መደበች　　2. ጀመረች　　3. ተከለች　　4. አወጣች

## መፃፍ

**ቃላቱን በመምረጥ ሳጥኖቹን በቅደምተከተል ሙሉ።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መቆፈር | ማለስለስ | መመንጠር | መመደብ | ቦታ መምረጥ |

የጓሮ አትክልት ቦታ አዘገጃጀት



ቦታ መምረጥ → ______ → ______ → ______ → ______

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ሐናና የምግብ ምርጫዋ**

**ሥዕሎቹን በዓረፍተነገር ግለጹ።**

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ምሳሌ፡- ዳስ ተሠርቷል። |  |
| 2. | |  |
| 3. | |  |
| 4. | |  |
| 5. | |  |

### መነጠልና ማጣመር

**የፊደላቱን ቦታ በማቀያየር ወይም በመቀነስ ሌሎች ቃላትን መሥርቱ።**


ምሳሌ፡- አስተሳሰረ → አሰረ፣ አሳ፣ አሰሳ፣ አረሰ፣ ሳተ፣ አሳተ፣ ተሳሰረ፣ አሳሰረ

1. አስለቀሰ
2. ብርቅርቅታ
3. አቀማጠለ
4. ደብረማርቆስ

# ግለንባብ

## የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎች ለጤንነት





የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎች ለጤንነት የሚሰጡት ጥቅም ብዙ ነው፡፡ የጓሮ አትክልትን በበቂ ሁኔታ መትከልና መጠቀም የቤተሰብን ጤንነት ለመጠበቅ ይረዳል፡፡ እንዲሁም ለሰውነት ጥንካሬን ይሰጣል፡፡ የአስተሳሰብ አድማስንም ያሰፋል፡፡ ስለዚህ ሰዎች በበሽታ እንዳይጠቁ ዘወትር አትክልትንና ፍራፍሬን መመገብ ይኖርባቸዋል፡፡

# 4ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

**ለጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡**

1. ከአትክልት ዓይነቶች ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ?
2. ከፍራፍሬ ዓይነቶች ውስጥ ሁለቱን ተናገሩ፡፡
3. ሥራቸው የሚበሉ ተክሎች ምን ምን ናቸው ?

## ቃላት

**ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡**

ምሳሌ፦ አጠጣ = ሰውዬው ተክሎችን ውሃ አጠጣ፡፡

1. መረጠ 2. አዘጋጀ 3. መነጠረ 4. ጠቀመ

## መፃፍ

| ? | ፤ | ፡፡ |
|---|---|---|

ሥርዓተነጥቦቹን በተገቢ ቦታ ፃፉ፡፡


1. ሃሊማ ጎበዝ ተማሪ ናት
2. ከገበያ ሽንኩርት ቃሪያና ብርቱካን ገዛሁ
3. አትክልትና ፍራፍሬ መመገብ የማይፈልግ ማን ነው

# 12ኛ ሳምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የግል ንጽህና አጠባበቅ**



### ቃላት

**በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።**


1. ማበጠር → ጠጉርን ሁልጊዜ ማበጠር አስፈላጊ ነው።
2. መበረሽ
3. መታጠብ

### ማጣመር

**ቃላትን በማጣመር ሌሎች ቃላትን መሥርቱ።**

ምሳሌ፡- ምክር ቤት

| |
|---|
| ምክር |
| ግምጃ |
| ፍርድ |
| ትምህርት |
| መፀዳጃ |



# ግለንባብ

## ታሞ ከመማቀቅ...



አንድ ቀን የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች፣ "ኧረ መምህር! ኧረ መምህር! ጓደኛችንን አመመው" እያሉ ጮኹ:: መምህራቸውም፣ "ወደተማሪው ዞር ብለው ምንህን አመመህ?" አሉት:: "ሆዴን! ሆዴን!" አለ:: ወዲያውኑ ወደ ጤና ጣቢያ ይዘውት ሄዱ:: ሐኪሙም ከመረመሩት በኋላ በንፅህና ጉድለት መታመሙን አረጋገጡ:: ከዚያም፣ "ይኸውልህ ዘወትር እጆችህን መታጠብ፣ ጥፍሮችህን መቁረጥ፣ ልብሶችህን ማጠብ፣ ጥርሶችህን መቦረሽ ወይም መፋቅ፣ ሰውነትህንና ጠጉርህን መታጠብ ይገባሃል" በማለት መከሩት፤ መድሃኒትም ሰጡት::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ::**

1. ተማሪዎች የጮኹት ለምንድን ነው?
2. ተማሪው የታመመው ለምንድን ነው?
3. እናንተ እንደተማሪው እንዳትሆኑ ምን ማድረግ አለባችሁ?

### ቃላት

**ዓረፍተነገር ሥሩ::**

ምሳሌ፦ ጠረን → የላብ ጠረን መጥፎ ሽታ ያመጣል::

1. ምግብ  2. በሽታ  3. መኝታ  4. ህመም

## መፃፍ

በስዕሉ ላይ የምታዩዋቸው ልጆች ምን እያደረጉ እንደሆነ በዓረፍተነገር ግለፁ::

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ፦ እጁን እየታጠበ ነው:: | |  |
| 1. | |  |
| 2. | |  |
| 3. | |  |

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የግል ንጽህና አጠባበቅ

## ቃላት

አባባሎችን በምሳሌው መሠረት በቃላችሁ መልሱ::

ምሳሌ፦ ጥርስ → ይቦረሻል ከተባለ

1. ጥፍር 2. ጠጉር 3. ሰውነት 4. ልብስ 5. እጅ

## መነጠል


የመጨረሻዎቹን ቅጥያዎች ከቃላቱ ነጥላችሁ ፃፉ::

ምሳሌ፡- አበጠረች → አበጠረ _ ች

1. አፀዳች 2. አነጠፈች 3. አለበሰች 4. አመጣች

## ግለንባብ

### የግል ንፅህና አጠባበቅ







የግል ንፅህናን መጠበቅ የዘወትር ተግባራችን ነው:: ሁልጊዜ ፊታችንን፣ እጆቻችንንና ሰውነታችንን መታጠብ፣ ጥርሶቻችንን መቦረሽ ወይም መፋቅ፣ ጥፍሮቻችንን መቁረጥ ያስፈልጋል:: ልብሶቻችንንም ማጠብና መተኮስ አለብን:: በተጨማሪም መፀዳጃ ቤታችንን በንፅህና መያዝ የዕለት ተዕለት ተግባሮቻችን ሊሆኑ ይገባል::

## 4ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

በጧት ተነስታችሁ የግል ንጽህናችሁን ለመጠበቅ ምን ምን ታደርጋላችሁ? ግለፁ::

1. መጀመሪያ 2. በመቀጠል 3. ከዚያ በኋላ 4. በመጨረሻ

## ቃላት

በክፍት ቦታዎች በምሳሌው መሠረት ተስማሚ ሐረጋትን ሙሉ።




## መፃፍ

በምሳሌው መሠረት ቃላቱን መድቡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውኃ | የጥፍር መቁረጫ | ሳሙና | የጥርስ ቡርሽ |
| ፎጣ | መስታወት | መፀዳጃ ቤት | ማበጠሪያ |
| መቀስ | ምላጭ | መርፌ | |

| በጋራ የምንጠቀምባቸው | በጋራ የማንጠቀምባቸው |
|---|---|
| መፀዳጃ ቤት | የጥፍር መቁረጫ |
| | |

# 13ኛ ሳምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**ንፅህና ለጤና**

### ቃላት

ዓርፍተነገር ፃፉ።

ምሳሌ፦ መሃረብ → ከድር አፍንጫውን በመሃረብ አፀዳ።

1. ቁጣ  2. ጉድጓድ  3. ጉንፋን

### ማጣመር

ክፍት ቦታዎችን በተስማሚ ፊደላት አሟሉ።

ምሳሌ፦ አ<u>ፀ</u>ዳ፣ አ<u>ረ</u>ዳ፣ አ<u>ገ</u>ዳ

| | | |
|---|---|---|
| 1. አ __ ረ | አ __ ረ | አ __ ረ |
| 2. አ __ ፈ | አ __ ፈ | አ __ ፈ |
| 3. አ __ መ | አ __ መ | አ __ መ |
| 4. አ __ በ | አ __ በ | አ __ በ |

### ግለንባብ

**“ትምህርትቤታችን ቤታችን ነው”**



ቀኑ ዓርብ ነው። እነሰይድ የመማሪያ ክፍላቸውን እየጠረጉ ጓደኞቻቸው ጠሯቸው። ቆሻሻውን ከክፍሉ በር ላይ ጥለውት ሄዱ። ሰኞ ጧት ስም ጠሪ መምህራቸው ሰይድን፣ ማርታንና ከበደን ጠሯቸው። በመቀጠልም “ትምህርትቤታችን እኮ ቤታችን ነው! ቆሻሻን በተዘጋጀለት ቦታ አስቀምጡ” በማለት መከሯቸው።